★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞክራሲያ ቅጽ** 36 **ቁጥር** 4 **ጥር** 2003 **ዓ.ም**

## <u>ኢትዮጵያና የታሪክ እንቆቅልሾች</u>

የታሪክ ምፀትና እንቆቅልሽ ሰለባዎች ከሆኑት በጣም ጥቂት የዓለም ሀገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ ሀገራችን አንዷ ነች ቢባል ማጋነን አይሆንም። ስለ ኢትዮጵያ ከልብ የሚያስቡ መልካም ዜጎች ይህንን ቢሉ፣ ለሀገራቸው፣ ለሕዝባቸው፣ ለታሪካቸው፣ ለወደፊት ዕድላቸውና ራዕያቸው ካላቸው መቆርቆርና መቆጨት እንጅ፣ የሞራል ሥልጣኑ የኛ ብቻ ነው ከሚል ግብዝነት እንዳይደለ፣ አርቆ አስተዋይ የሆነ ዜጋ ሁሉ ይገነዘበዋል። ያለፈ ታሪካቸውን በሚገባ አውቀው አሁን ያሉበትን ተጨባጭ ሁኔታ ተረድተውና ሀገራቸው አሁንስ ወዴት አቅጣጫ እያመራች ነው? የሚለውን አስጨናቂ ጥያቄ በቅጡ ተገንዝበው፣ ብሔራዊ መፍትኄ ሊኖር ይገባል ብለው የሚያስቡ አርቆ ተመልካች ዜጎች ሁሉ፣ በመፍትኄው ፍለጋ ላይ መረባረብ እንዳለባቸው በአግባቡ ይረዱታል። ይህንን በሙሉ ልብ ለመናገር የደፈርነው ለተተኪው ትውልድ፣ ብሔራዊ ችግርና ድኅነት አውርሶ ማለፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምኞቱና ፍላጎቱ እንዳልሆነ በሚገባ በመረዳታችን ብቻ ነው።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ እኛ ብቻ እናውቅለታለን ከሚሉት ዕብሪተኞችና ፈሪሳውያን የሚለየን መሠረታዊ ጉዳይ አንዱ፣ ለምንታገለለት ሕዝብ፣ የችግሩ ተካፋይ በመሆን በጥቃቱና በበደሉ ወቅት ከጎኑ በመቆማችን እንጅ፣ ለሀገራችን ችግሮች ሁሉ፣ መፍተኄው ለእኛ ብቻ የተከሰተ ነው ከሚል ከንቱ - ውዳሴና የምርጥነት ስሜትም አይደለም። በመሠረቱ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ እኛ ብቻ እናውቅልሀለንና አሜን ብለህ፣ ተቀብለህ ተገዛ ማለት ከድንቁርና የመነጨ ትዕቢት ነው። በዕርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየጊዜው በሚፈራረቁ አምባገነኖች ተበድሏል፣ ተጠቅቷል፣ ግፍና መከራም ዘንበውበታል። ከዚህም የተነሳ፣ ቁጭት፣ ምሬትና ሰቆቃ አለበት። ይህንንም የሚገነዘብለት የቅርብ ጎረቤትም ይሁን የሩቅ ዘመድ እንደሌለውም እንገነዘባለን። ለዚህም ነው፣ የሀገራችንን ችግሮች ሁሉ መፍታት የሚገባን እኛው ራሳችን ኢትዮጵያውያን መሆን አለብን ብለን የምናምነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የቅርብ ጎረቤትም ይሁን የሩቅ ዘመድ እንደሌለው ተገንዝበው፣ የሚያምናቸው መሪዎቹ በየጊዜው ይጎዱታል፣ ይበድሉታል፣ ያዋርዱታል፣ ይጨቁኑታል፣ ይዘርፉታልም። በመጨረሻም አልሆን ሲላቸው ከድተው፣

ለአዲስ አምባገነን ገዥዎች በማጋለጥ ጥለውት ይሄዳሉ፡፡ በቀውጢ ቀን፣ በወሳኝ ጊዜ፣ ሰማይ ምድሩ በሚደፋበት ወቅት፣ ጥለውት ይሸሻሉ፡፡ የአምባገነን ሥርዓት አራማጆች በሥልጣን በሚቆዩበት ዘመን፣ ተጠልቶ መፈራትን እንጅ፣ ተወዶ መከበርን አይፈልጉም፡፡ ዘወትር በሕዝብ ዘንድ የተጠሉ መሆናቸውን ባይዘነጉትም፣ ዘለዓለም ተፈርተው የሚኖሩ ይመስላቸዋል፤ ሁል ጊዜ ሕዝቡ ፀጥ-ለጥ ብሎ የሚገዛላቸውም ይመስላቸዋል፡፡ ኃይላቸው የሚከስም፣ ጉልበታቸው የሚደክም፣ ሥልጣናቸው የሚወድም፣ ቀናቸው የሚጨልም፣ ጊዜያቸው የሚያከትም ፈፅሞ አይመስላቸውም፡፡ በሕዝብ አመፅ በአፍ-ጢማቸው የሚደፉ መሆናቸውም ጭራሽ አይታያቸውም፡፡

የሕዝብ ኃይልና ሥልጣን፣ የኅብረተሰብ ዕድል የመጨረሻው ወሳኝ መሆኑ የሚያከራክር ባይሆንም፣ በኢትዮጵያ ሀገራችን ግን ይህ ሐቅ እስከዛሬ ድረስ መከሰት ቀርቶ፣ ሊታለምም አይገባውም ሊሉ የሚቃጡ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ህልምን ወደ ዕውነት ለመለወጥ ግን ሕዝቡ የሚሳነው አይደለም፡፡ ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨምግጎ ከያዘው አባዜ ሲላቀቅ ብቻ ይሆናል፡፡ ይህ አባዜ ደግሞ፣ የታሪክ ዕንቆቅልሽና የዘመናት ምፀት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ከማያቋርጥ አዙሪት ለመውጣት፣ እነኝህን ቁራኛዎች ማስወገድ መቻል ይኖርበታል፡፡ ከአምባገነን አገዛዝ ሥርዓት አዙሪት ለመላቀቅ ዋስትናው፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት በኢትዮጵያ ሕዝብ እጅ መግባቱን ማረጋገጥ ነው፡፡ ለዘመናት ከባዕድ ወረራ ነፃ ሆኖ የኖረ ሕዝብ፣ በአገር-በቀል አምባገነኖች መገዛቱ፤ የተፈጥሮ ሀብት ሞልቶ ተርፎት በድኅነት መማቀቁ፤ በዓለም የሚታወቅ ምቹ የአየር ጠባይ፣ ድንግልና ለም መሬት ተትረፍርፎለት ከረሃብ ቁራኛነት አለመላቀቁ፤ በቂ የተማረ- የሠለጠነ የሰው ኃይል እያለው፣ ከበሽታና ከመሃይምነት ማነቆ አለመውጣቱ፤ የረዥም ዘመን አኩሪ ታሪክ ባለቤት ሆኖ ሳለ፣ በታሪኩ እንዲያፍር እስከመገደድ ድረስ መድረሱ፤ የተከበሩ እምነቶች/ሃይማኖቶችና ባኅሎችን እያስተናገደ አብሮ የኖረ ሕዝብ መሆኑ እየታወቀ፣ ይህንን ለመበጥበጥና ፍቅሩን ለማፍረስ ጥረት መደረጉ፤ በአሁኑ ወቅት ያለበትን አሳዛኝ የቀውስ ሁኔታ የሚገልጥ ሆኗል፡፡ የአንድ ብሔር ነፃ አውጭ ድርጅት ነኝ የሚል ቡድን የኢትዮጵያን መንበረ-ሥልጣን ይዞ፣ የኢትዮጵያን አካል እየቆራረሰ፣ ዜጎቿንም እየከፋፈለ፣ ሀብትና ንብረታቸውንም በጭካኔ እየዘረፈ፣ የባዕዳንን ጥቅም ለማስጠበቅ የቆመ የኢትዮጵያ ጠላቶች አገልጋይ የሆነን የከሃዲ ስብስብ በሥልጣን ቦታ ከማየትስ የበለጠ ምን ምፀትና እንቆቅልሽ ይኖራል?

የሙሶሎኒ ጣሊያኖች የአድዋን ችንፈታቸውን ለመበቀልና ኢትዮጵያን ቅኝ ለማድረግ ያደረጉት የ1928-ቱ የማይጨው ወረራ በሀገራችንና በህዝባችን ላይ ይህ ነው የማይባል ጉዳት ማድረሱ የተመዘገበ ነው፡፡ ታዲያ አንዳንዴ ነገሮችን በጥሞና ስናስተውል፣ ይህ የውጭ ወራሪ ኃይል ለዓላማው መሳካት የተጠቀመባቸውን አንዳንድ ነገሮችን ሀገር በቀል የሆነው ወያኔም ሲጠቀምባቸው ማየታችን ያለንበትን ሁኔታ ክፉነት ያሳያል፡፡ ጣሊያኖቹ የኢትዮጵያን

ሕዝብ፣ በኀሳና በሃይማኖት ለመከፋፈል እንደጣሩት ሁሉ፣ ወያኔም ዜጎቻችንን በዘርና በቋንቋ ለመከፋፈል በከፍተኛ ትጋት ላይ ታች ሲል ዓመታት አልፈዋል። ሰንደቅ ዓላማችንን ጨርቅ ነው እያለ ሲያጣጥል ታዝበናል። እንዲያዉም ክፋቱን የሚያጎላው፣ ቢያንስ የኢትዮጵያን አንጡራ መሬት፣ ጣሊያኖች ለሱዳን አሳልፈው ሰጥተዋል የሚል ሰነድ እስካሁን አለማንበባችን ነው። የሚያስገርመው ግን ይህ የዛሬው ትውልድ፣ የባዕዳን ቅኝ ገዥዎች ሳይሆን የአገር- በቀል ከሃዲያን ተጠቂ መሆኑ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ከነኝህ ቁራኛዎች ሊላቀቅ የሚችለው፣ ሁሉን ማድረግ የሚያስችለው ኃይልና ሥልጣን ሊኖረው ሲችል ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ፣ ከላይ የተዘረዘሩትን የታሪክ እንቆቅልሾችንና ብሔራዊ አባዜዎችን አስወግዶ የራሱን ነፃ ሥርዓተ-መንግሥት ሊመሠርት የሚያስችለውን ሁኔታ በመፍጠር የሚፈልገውን መንግሥት ሲመሠርት መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም። ይህንንም ለማድረግ የሚችለው ደግሞ፣ የአጋንንቱን ማሰሪያ ሳጥኑን የከፈተውን የዘረኛውን ሥርዓት ሲያስወግድ ብቻ ይሆናል። በዕርግጥ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአምባገነኖች አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻው ነፃ የሚሆነው፣ ከባድ መሥዋዕትን የሚጠይቅ ትግል ሲያካሂድም ብቻ ነው። ራሱን በራሱ ነፃ ያላደረገ ሕዝብ፣ ማንም ነፃ እንደማያደርገው ከኢትዮጵያ ሕዝብ የበለጠ የሚያውቅለት ከቶ አይገኝም። ምነው ቢሉ፣ በረዥም አኩሪ ታሪኩ ሂደት በድርጊት አስመስክሯልና የሚል ይሆናል መልሱ።

የኢሕአፓ የትግል አልፋ-ኦሜጋ የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅም መጠበቅ በመሆኑ፣ የዚህ ተፃራሪ የሆነውን ሁሉ የሚፋለመውም ከዚህ መተከላዊ አቋም በመነሳት ነው - ሌላ ምንም ነገር የለውም። የሀገርና የሕዝብ ደመኛ የሆነን ሥርዓት፣ በምንም መልክ፣ ቅርፅና ይዘት ቢመጣ ማስወገድ፣ የሕዝብ የዜግነት ብቻ ሳይሆን፣ የተፈጥሮ መብቱ መሆኑን መረዳት ለአንድ ሀገር ዜጋ መሠረታዊ መሆኑን በአንክሮ ያምንበታል። በዚህ ምክንያት፣ የትግሉን መነሻና መድረሻ ከሕዝቡ መሠረታዊ መብትና ፍላጎት ጋር ማቆራኘቱ አያስደንቅም። ከአፄው ሥርዓት ጀምሮ ከዚያም በኋላ የተለዋወጡትን አምባገነን ሥርዓቶች እየተፋለመ የሚቃወማቸው በዚህ ፅኑ ዕምነቱና በማይበገረው ቃል-ኪዳኑ ብቻ ነው። ዓላማን ከዕምነት፣ ቃል-ኪዳንን ከመሥዋዕትነት፣ ራዕይን ከፅናት ጋር አዋህዶ መታገሉ፣ እንዲሁም፣ የሀገርና የሕዝብ ፍቅርን፣ ከድርጅት ፍቅር በላይ ማስቀደሙ፣ የኢሕአፓ ማንነት መለያው ሆኖ ቆይቷል። ወደፊትም ይኸው ሆኖ ይቀጥላል።

የአምባገነን ሥርዓት አራማጆች የመጀመሪያው ጥፋታቸው፣ የማንኛውም ሀገር ዜጋ ቢሆን፣ በግል መብቱና በሀገሩ ነፃነት ከመጣ ማንንም ኃይል ሁሉ የሚቃወምና የሚዋጋ መሆኑን አለመረዳታቸው ነው። እንደምንም ተብሎ አንድ ጊዜ የመንግሥት ሥልጣን በእጃችን ይግባ እንጅ፣ የመጨቋኛ መሳሪያዎችን ሁሉ እየተጠቀምን፣ ተቃዋሚውን ሁሉ እየከፋፈልን

በማጥፋት፣ ሕዝቡን ፀጥ-ለጥ አድርገን መግዛት እንችላለን፣ የሚለው የአምባገነኖች የጋራ ባኅሪ ነው:: ይህም ባኅርይና ድርጊት ለተወሰነ ጊዜ እንደሚጠቅማቸውም እስካሁን ድረስ ከማንም ዜጋ የተሰወረ አይደለም:: ምክንያቱም፣ ደርግ ለአስራ ሰባት፣ ወያኔም ለአስራ ዘጠኝ ዓመታት በሥልጣን ላይ እንዲቆዩ ያስቻላቸው፣ ይኸ የአገዛዝ ስልታቸው በመሆኑ ነው:: በአምባገነን ሥርዓት አራማጆችና በዴሞክራሲ ኃይሎች መካከል ብዙ መሠረታዊ ልዩነቶች መኖራቸው እንዳለ ሆኖ፣ የመንግሥት ሥልጣን መመንጨት ያለበት ከየት ነው የሚለው ቁልፍ ጥያቄ ግን የሰማይና የምድርን ያህል ያራርቃቸዋል::

ዛሬ ሀገራችን በረዥም ታሪኳ አጋጥሟት ከማያውቅ ብሔራዊ ችግር ውስጥ የገባች ቢሆንም፣ በእኛ ዕምነት፣ ሀገራችንንም ሆነ ሕዝባችንን ለአንዴም ለሁሌም የሚያላቅቀው መፍትኄ ከራሱ ከሕዝቡ የሚፈልቅና በሕዝቡ ቁጥጥር ሥር ያለ ለመሆኑ አንጠራጠርም:: ይህን ለማለት የቻልንበት በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ነው:: አንደኛው፣ በየጊዜው፣ ታሪኩን፣ ነፃነቱንና ሀገሩን ሊቀሙት የመጡትን ባዕዳን ወራሪዎች እየተዋጋ በመመለስ፣ ለነፃነቱ ቀናዒ መሆኑን ያስመሰከረ ሕዝብ ስለነበር ነው:: ይህ ሐቅ፣ ዛሬም እንደትላንቱ የገጠመውን ችግር ለመፍታት የሚያስችለው ዘዴና ኃይል የራሱ አንጡራ ሃብት እንደሆነ ያረጋግጣል:: ሀለተኛው፣ ካለፉት ረጅም ዓመታት ጀምሮ በተለያዩ ምክንያቶችና ሁኔታዎች እርስ በእርሱ እንዲከፋፈል፣ እንዲፋጅና እንዲበታተን የተደረገበትን ጫና ሁሉ በመቋቋም የጋራ ጠላቶቹን ሴራ ሁሉ ያከሸፈ በመሆኑ ነው:: እስካሁን ያለው ሐቅ ይህ ቢሆንም፣ ወደ ፊትስ ይህ የብሔራዊ አንድነትና የጋራ ጠላትንም ሴራ ሁሉ በጋራ የመቋቋም ችሎታ እንዳለ ለመቀጠሉ ምን ዋስትና አለ የሚለው አቢይ ጥያቄ ግን የሁሉም ዜጋ ጭንቀትና ስጋት እንደሆነ በማንኛውም ዜጋ አዕምሮ ውስጥ የሚውጠነጠን ኃሳብ ነው::

የሀገራችን የፖለቲካ መልክዓ-ምድር በማያጠራጥር መልኩ መለወጡን ሲያውቁ፣ የሕዝብ ትግል ማየሉንም ማየት ሲገደዱ ወያኔን ሲረዱ የነበሩት ባዕዳን ሁሉ፣ ከመቅፀበት ወያኔን ከድተውና አጋልጠው፣ ጥቅማቸውን በዘለቄታ መልኩ ሊያስጠብቁበት ወደሚያስችላቸው አዲስ ምዕራፍ በመሸጋገር ሰልፋቸውን ለማስተካከል ይሽቀዳደማሉ:: ይኸን የሚያደርጉትም፣ ዘላቂ ጥቅምን ማስጠበቅ እንጅ፣ ለጊዚያዊ ወዳጅ መጨነቅ የሚባል ስለማይኖራቸው ነው:: ከዚህም በቀር፣ የዓለም አቀፍ ግንኙነትም ሆነ በሀገሮች መካከል የሚካሄደው ዲፕሎማሲ ትኩረቱና ጥድፊያው በጊዚያዊ ጥቅሞች ዙሪያ ያጠነጠነ ስለሆነ፣ የአምባገነኖች ዘላቂ ወዳጅ ከቶ ሊሆን አይችልም:: የአንድ ሀገር ሕዝብ፣ መፃዒ ዕድሉን የሚወስነው ያው ዞሮ ዞሮ ራሱ ስለሚሆን፣ የውጭ ጣልቃ-ገብነትም ሆነ፣ የባዕዳንን ጥቅም አስጠባቂ የሆኑት የውስጥ ቅጥረኞች፣ የሕዝቡን መራራ ውሳኔ ሊያቆሙት አይችሉም:: ይኸም በታሪክ ተደጋግሞ የታየ ስለሆነ ብዙ ገለፃ የሚያስፈልገው አይደለም:: ሰሞኑን በቱኒዝያ ሕዝባዊ አመፅ፣ ሀገሪቱን ለሃያ ሦስት ዓመታት ጨቁኖ ሲገዛ የነበረው ፕሬዝዳንት ከሀገር ሲባረር፣ መጠጊያ ስጡኝ

ያላቸው ወዳጁ የነበሩ መንግሥታት ሊያስጠጉትም ሆነ ሊያድኑት አለመፍቀዳቸውና አለመቻላቸውን ታዝበናል። እስከናካቴውም የሕዝብን ኃብት ዘርፎ በባዕድ ሀገር በሚገኙ ባንኮች ያስቀመጠውን ገንዘብ አንዳንድ የአውሮፓ ሀገሮች እንዳይንቀሳቀስ ሲያግዱ ሌሎቹም (በአውሮፓ ሕብረት ደረጃም) ተመሳሳይ እርምጃ ለመውሰድ በአደባባይ እየተናገሩ ነው። ይኸም የሚያስረዳው፣ አምባገነኖች ቀን ሲከዳቸው ማንም እንደማይቆምላቸው ትኩስ ማስረጃ ለመጠቆም እንጂ የኖረና የታወቀ ሐቅ ነው። ይህ ተመሳሳይ መፃዒ ክስተት በሀገራችን በኢትዮጵያ መከሰቱ የማይቀር ለመሆኑ ብዥታ ባይኖርም፣ ያ ክስተት እንዲመጣ ለማድረግ የወያኔን ዕድሜ ለማሳጠር የሚታገለው ሁሉ የየድርሻውን መሥዋዕት መክፈል ግዴታው እንደሆነ ሊገነዘበው ይገባል። ኢሕአፓ በበኩሉ፣ ሁኔታውን ባግባቡ እየተጠቀመ ግዴታውን ለመወጣት እየጣረ ነው።

በሌላ ገፅታው ሲታይ ደግሞ፣ ለአንድ አምባገነን ሥርዓት የመጨቆኛ መሳሪያ ሆነው የሚያገለግሉትን ተቋማት ሁሉ አዋቅሮ መቆጣጠሩን መገንዘብ ያስፈልጋል። ለዕድሜ መቀጠያ፣ ለሥልጣኑ ማጠናከሪያና ለሕዝብ መጨቆኛ የሚያገለግሉትን መሣሪያዎችና ተቋማትን አዘጋጅቶ ይቆጣጠራል። የሀገሪቱ ስም ሽፋን የተሰጠው ሠራዊት ከላይ እስከታች የተዋቀረው በአብዛኛው ከአንድ ብሔር ከመጡ አዛዦች ሥር መሆኑ የአደባባይ ምሥጢር ከሆነ ቆይቷል። ፀጥታው፣ ፍርድ ቤቱ፣ የፖሊስ ድርጅቱ፣ ፕሮፓጋንዳውና የመገናኛ ብዙሃኑ ሁሉ በአንድ ላይ የተዋቀሩት የወያኔን ሥልጣን ለማጠናከር፣ የዘረኛውን ሥርዓት ፖሊሲ ለማራመድና ለመጠበቅ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። በመላው ሀገሪቱ የተገነቡት በርካታ እስር ቤቶችና ማጎሪያ ቦታዎች ሁሉ አግልግሎታቸው፣ የወያኔ ተቃዋሚዎችን ለማሰቃየትና ለማፈን መሆኑን የዓለም አቀፍ ተቋማትና የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ ድርጅቶች ሳይቀሩ በዘገባቸው ያረጋገጡት ሐቅ ሆኗል። ወያኔ ከዚህ አልፎ ተርፎ ዋና ዋና የገንዘብ ምንጮችን ተቆጣጥሯል። ባንኮችን፣ የውጭና የውስጥ ንግዶችን፣ የመገናኛና የመጓጓዣ አውታሮችን ሁሉ በእጁ አስገብቶ የሀገሪቱን ብሔራዊ ሀብት በብቸኝነት ለመቆጣጠር አስችሎታል። የዚህ ዐይን አውጣ ዘረፋ ዋነኞቹ ደግሞ መለስ ከነባለቤቱ መሆናቸው የታወቀ ነው። ሕዝባዊ ቁጣ ከፈነዳና ሕዝባዊ አመፅ ከተቀጣጠለ እነዚህ ሁሉ ባጭር ጊዜ ውስጥ በሕዝቡ ቁጥጥር ሥር ውለው ለሕዝብ አገልጋይ ይሆናሉ። በሕዝብ ላይ ወያኔ እያደረሰ ያለው ፈርጀ ብዙ ሰቆቃ ምስጢር አይደለም። ግብረ ስየሉ፣ ግፉ፣ ረሀቡ፣ መጠለያ ማጣቱ፣ የኑሮ ውድነት፣ ሙስናው፣ ሕፃናት ላይ የሚደርሰው በደል፤ ለዘመናዊ ባርነት ለባዕድ መሸጡ፤ በሴቶች ላይ የከፋ በደል መፈፀም መቀጠሉ፤ ሕዝብን እርስ በርስ በብሔረሰብና ሃይማኖት ልዩነት መሠረት ማጫረሱ አላማባራቱ፤ በሕዝብ ላይ ፍጅትን መፈፀም የአገዛዙ መለያ ሆኖ መገኘቱ፤ የሕዝብ መሬት ለባዕዳን መስጠቱ ፤ ከቀዬው ሕዝብ መፈናቀሉ፤ ...ወዘተ፣ ወዘተ-- ግፉ ሞልቶ ተርፎ ፈስሷል። ከዚህ በላይ ምን እየተጠበቀ ነው እያሰኘም ነው። በርግጥም "ምንስ እየተጠበቀ ነው?" የሚለው ጥያቄ ሕዝባዊ መልስ የሚያሻው ነው።

ነገ ከሚመጣው አርዕድ-አንቀጥቅጥ ሕዝባዊ አመፅ አንፃር የጭቆናውና የግፍ አገዛዙ ዕዋ ሞልቶ ሲገነፍል የሕዝብን አመፅ የሚያቆመው ኃይል ሊኖር አይችልም። ይህም የሚሆነው ለሕዝባዊ አመፅ ምዕራፍ ከፋች የሆኑት መሠረታዊ ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል። ከነዚህ አበይት ሁኔታዎች መካከል፣ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች በወሳኝነት ይጠቀሳሉ። እነርሱም፣ ጨቋኙ ሥርዓት እንደለመደው እየጨቆነ መግዛት ሲሳነውና የሚጨቆነው ሕዝብ ደግሞ፣ ከእንግዲህ ወዲህ አልጨቆንም በማለት አምርሮ-አምፆ ሲነሳ ነው። ወቅታዊው የሀገራችን ሁኔታ በግልፅ የሚያሳየው ጉዳይ ቢኖር፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የግፍ አገዛዙና የመከራው ዕዋ ሞልቶ እየገነፈለ በመሄድ ላይ መሆኑ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ጉዳይ፣ በዓለም ላይ የሚካሄደው የዴሞክራሲ ለውጥ እንቅስቃሴ፣ ወላፈኑ ወደ ሀገራችን ዘልቆ የሚገባበት ዕውነታ ይሆናል። ዘገዩም ፈጠኑ፣ እነኝህ ሁለት የለውጥ ምዕራፍ ከፋቾች በሀገራችን የፖለቲካ መልክዓ-ምድር ላይ የውኅደት አዋጅ አብስረው የለውጥ ምዕራፍ የሚከፈትበት ወቅት ሩቅ አይሆንም። የወያኔ አገዛዝ የቀብር ደወል በመላ ኢትዮጵያ ተሰምቷል--ቀብሩ ይጣደፍ ዘንድ በጋራ እንጣር፤ እንታገል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ የዴሞክራሲ ትግል!